# ቀጣዩ ተግባር ምን ይሁን?

አንተነህ ሽፈራው (እ.ኤ.አ ጁላይ/July 12, 2010)

በምርጫው ለመሳተፍ ወስነው የነበሩ ተቃዋሚዎች ለረጅም ጊዜ ሲጠብቁት የነበረውን የወያኔ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ብሔራዊ የምርጫ ተውነት ውጤት እጅግ አስገራሚ በሆነ መልኩ መጠናቀቁን ካየን ሳምንታትን አሳለፍን። ነገሩ "ጅብ ከሄደ ውሻ ጬኽ" እንዲሉ መሆኑ ነው የሚያሳዝነው እንጅ እውነተኛ ተቃዋሚ የሚባሉት ምርጫ ውስጥ የሚገቡ ከሆነ መጀመሪያ ማከናወን የነበረባቸውን ተግባሮች በሩቅም ሆነን ለማመላከት ከመሞከር አልቦዘነም ነበር። ለአብነት ያህል ------------------ "የብልሁን የሊጋባ በየነ ስልት እንጠቀም" በሚል ርዕስ http://www.quatero.net/pdf/ye_ligaba_beyene_silt_Feb17_2010.pdf, February 17, 2010 በወጣ ጽሁፍ አንድነት ከመድረክ ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት በመጠቀም ከመኢአድ ጋር መቀራረብ የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሮ በግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ሊደረግ በታሰበው ብሔራዊ ምርጫ በጋራ በመሆን አንድ "አገር አድን" መለስተኛ ፕሮግራም በመንደፍ ወያኔን በምርጫው ሂደቶችና ተግባሮች ላይ ከወዲሁ አስቀድሞ በሚገባ አጥብቆ የመያዝን ወሳኝነት ለማስጨበጥ የሞከርኩ።

በተለይም ደግሞ ዶ/ር ነጋሶ ወደ ሕብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት በመምጣት አንድነትን መቀላቀላቸው እጅግ በጣም የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም ቅሉ ከአንድ ድርጅት ሰውነት/አባልነት ይልቅ *በኢትዩጵያዊ ጨዋነት አቀራረብ መሠረት አንድነትንና መኢአድን ከዚያም መድረክን ለማቀራረብ የሽምግልና ስራ ሰርተው በግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ሊደረግ በታሰበው ምርጫ ተቃዋሚው የወያኔን ሁለንተናዊ የማምታታት ሂደት/ድርጊት በብቃት መመከት እንዲቻል* ያልተቆጠበ ጥረት እንዲያደርጉ ወገናዊ ጥሪ ገና በፌብረዋሪ/February 17, 2010 ለማድረግ ሞክሬ ነበር። ሆኖም ግን ያ መደረግ የነበረበት በጣም ወሳኝ ጥረት ሳይደረግ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን መድረክና መኢአድ በምርጫው ዝግጅት ዙሪያና አካሄድ ላይ እጅግ በጣም የማይቀራረብ አቋም ይዘው ቀረቡ።

እዚህ ላይ አንድ ከግራ ቀኙ በኩል መጨበጥ የነበረበት ቁም ነገር ቢኖር የምርጫ ስነምግባር በሚባለው ሰነድ ላይ መወያየቱ ሊጠቅም ይችል የነበረው መጀመሪያ ነገር የወያኔ ሕገ-መንግሥት በራሱ በወያኔ የሚከበር ቢሆን፤ ነፃና ፍትሃዊ ፍርድ ቤትና ለሕገመንግሥት ተገዥ የሚሆን ፖሊስና ብሔራዊ የአገር መከላለያ ሠራዊትና ነፃ ጋዜጦች ያሉን ቢሆን ነበር። ከላይ በአጭሩ የጠቀስኳቸው ዐብይ የአገር ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በለሉበት አገር ውስጥ ስለ የምርጫ ስነምግባር በሚባለው ሰነድ ላይ ለመወያየት መሞከር ራስን ለማታለል ካሎሆነ በስተቀር ምንም የሚፈይደው ቁም ነገር እንደሌለ ከላይ February 17, 2010 ብዬ በጠቀስኩት ጽሁፍ ግልጥ ለማድረግ ከመሞክር ጎን ለጎን ይልቁንስ መድረክ በተናጠል ከወያኔ ጋር ለመደረደር ከመጠየቅ በምርጫ ጉዳዮች ላይ ከመኢአድ ጋር በመቀራረብ ጠንካራ የጋራ የመከራከሪያ አቋም ይዘው በመቅረብ ወያኔን አስቀድመው በጋራ መቋቋም እንዳለባቸው ለማመላከት ሞክሬ ነበር።

በዚህ ረገድ መኢአድ የምርጫ ስነምግባር በሚባለው ሰነድ ላይ ከወያኔ ጋር ለመደራደር ከመፈለግ አልፎ ተርፎ በስነምግባር ድርድሩ ላይ የተደረሰባቸው ስምምነቶች በአገሪቷ እጅግ በጣም በዓይነቱ ታይቶ ያልወቀ አዲስ ሰላማዊ የፖለቲካ ብሂል ተፈጠረ በሚል ድርድሩን በማወደስ አቋሙን ግልፅ እስከማድረስ ድረስ ሲሄድ መድረክ ደግሞ የምርጫ ስነምግባር በሚባለው ሰነድ ላይና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ለመደራደር ከወያኔ/ኢህአደግ ጋር የተናጠል ድርድር ለማድረግ አጥብቆ ጠየቀ።

መድረክ ወያኔ ሳይሆን ኢህአዴግ ከሚለው ጋር የተናጠል ድርድሩን ከመጠየቅ አልፎ ተርፎ "ፍየል ከመምጣቷ ቅጠል መበጠሷ" እንዲሉ አዲሱ የአንድነት ከፍተኛ አመራር አቶ ሰዬ አብርሃ sne_migbar_sillu_Nov16_2009 በሚል ርዕስ ባቀረበው ፅሁፍ መኢአድን በጎሣ ድርጅትነት እስከመወንጀል ድረስ እጅግ በጣም ርቆ ሄደና ቢያንስ ቢያንስ በምርጫው ዙሪያ እንኳ የመድረክና መኢአድ የመቀራረብን ተስፋ ጭራሹኑ አበላሹትና ወያኔ ይበልጥ ማምታታት የሚችልበትን መንገድ ራሳቸው ሁለቱ ድርጅቶች አመቻቹው ሰጡት። እኔን እጅግ በጣም የገረመኝ ደግሞ እነ ፕ/ር አሥራት ወ/የስ በወቅቱ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) በሚል ስያሜ ድርጅት እንዲመሰርቱ የተገደዱበት ዋናው ምክንያት ያውም በራሳቸው በአቶ ሰዬ አብርሃና መለስ ዜናዊ ወያኔያዊ አቋም አስገዳጅነትና ድርጊት መሆኑን በሚጋባ ጠንቅቀው እያወቁ ያን ማለታቸው ነው!!!

በጣም የሚገርመው ግን ምንም እንኳን መድረክና መኢአድ ከምርጫው በፊት የጎሪጥ ይተያዩ የነበር ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን ሁለቱም የወያኔ የቅጽፈት ምርጫ ሰለቦች ከመሆን አለማምለጣቸው ነው። ይህንንም ተመሳሳይ የወያኔ የምርጫ ሰለባነት ግምት ውስጥ አስገብተውና ቅድሚያ ለሚሰጠው አገራዊ የሕዝብ ጥሪ የበለጠ ቦታ በመስጠት ***በግንቦቱ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫ ውጤት ሕገወጥነት*** ላይ ሁለቱ ኃይሎች ጠንካራ ተከራካሪ ለመሆን እንዲችሉ አንድ የተቃዋሚዎች የጋራ የአስቸኳይ ጊዜ ኃይል መፍጠር የግድ ይላል በሚል Form An ***Emergency Grand Coalition Force*** “Let Us Seize This Crucial Moment” በሚል May 28, 2010 በወጣ ፅሁፍ በግል ለማመላከት የሞከርኩ። http://www.quatero.net/pdf/let_us_seize_this_crucial_moment.pdf

ይህ አንገብጋቢና መሠረታዊ የሕዝብ ጥሪ መታለፍ የሌለበት ቢሆንም ቅሉ እስካሁን ድረስ ከመድረክ ይሁን ከመኢአድ አመራሮች ጆሮ ሊደርስ እንዳልቻለ የተመለከትነው በመሆኑ ይህንና የወያኔን የምርጫ ቅፅፈት ለጊዜው በዚህ አልፈውና በዚህ ፅሁፍ የበለጠ ለማየት ወደ ምፈልገው ሌላ ችግር ልውሰዳችሁ። - - አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) ዙሪያ ባሉ የውስጥ ችግሮችና የግልን የመፍትሔ ሓሳብ ለማመላከት ያህል። ቀጣዩም ትግል ይህን መሠረት ያደረገ ምሆን ይኖርበታል።

## 1. በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (በአንድነት) ዙሪያ ባሉ የውስጥ ችግሮችና የግልን የመፍትሔ ሓሳብ ለማመላከት ያህል።

መጀመሪያ ነገር በዚህ ዙሪያ የምለው ሁሉ የግል አስተያየት በመሆኑ ምንም ይሁን ምን አቀራረቤ ከአስተያየትነት ሊያልፍ አይችልም። ከዚህ አኳያ የሚጠቀመውን ሓሳብ መውሰድና የማይፈልጉትን ደግሞ መተው የራሱ የአንድነት ፓርቲና የአባላቱ ብቸኛ ሕጋዊ መብት ይሆናል። በተደጋጋሚ ጊዜ ስለአንድነት የውስጥ ችግሮች ሁኔታ የግል የመፍትሔ አስተያየት እንድዘረጋ የሚገፋፉኝ ግን በአንፃራዊ መልኩም ቢሆን አንድነትንና መሪውን ብርቱካንን ከሌሎች የአገር ውስጥ ካሉ ድርጅቶች በበለጠ በበጎ ዐይን የምመለከትበት ሁለት ሁነኛ ምክንያቶች ስለአሉኝ እንጅ በሌላ ድርጅት የውስጥ ድርጅታዊ ጉዳይ ውስጥ ዘሎ ለመግባት ካለ ፍላጎት የመጣ አለመሆኑ ግን በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲያዘበት እፈለጋለሁ። ሁነኛ ምክንያቶቼ ካልኳቸው ውስጥ ለአብነት ያህል ለመጥቀስ፡-

1ኛ. የአንድነት አደረጃጀት ከመጀመሪያው ጀምሮ በባሓሪው፤ በአደረጃጀቱና በሥያሜው ሕብረብሔራዊ አፈጣጠር/አደረጃጀት ያለው በመሆኑ፤

2ኛ. ብርቱካን በቅንጅት ድርጅታዊ ቆይታዋ ወቅት/ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ አመኔታ የጣለበትን ቅንጅትን “ለግል ጥቅሟ ወይም ርካሽ ዝናዋ” ስትል አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት በግሏ ፈፅማለች የሚል እምነት ስለሌለኝና እንዲያውም በሂደት ብርቱካን ለቆመችለት ዓላማዋ/እምነቷ በፅናት የመቆም ፅኑ እምነት እንዳላት በተግባር በማሳየቷ ናቸው።

በአንድነት ውስጥ የውስጥ ችግር እንዳለ ስናወሳ መጀመሪያ ማወቅ ያለብን የውስጥ ችግሮች መከሰት ምክንያቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በትክክክል ለይቶ ለማወቅ መሞከር ለመፍትሄ አፈላለጉ እጅጉን ይረዳል። ከዚህ አንጻያ በእኔ እምነት ለችግሮች መከሰት ዋነኛ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን በጥቅሉ እንደሚከተለው ላስቀምጥ፡-

1ኛ. በሓሳብ/በአመለካከት ልዩነቶች ላይ "ድርጅታዊ ፕሮግራምንና ውስጥ ደንብን" መርህ ባደረገ መልኩ ደህና አድርጎ መወያየት የሚያስችል ሰፊና ዴሞክራሲያዊ የውስጥ መድረክ አመራሩ የማይፈጥር ከሆነ ወይም ከሌለ፤

2ኛ. በሰፊና ዴሞክራሲያዊ የውስጥ ውይይት/ቶች በብዙሃን ውሳኔ ላለፉ ድርጅታዊ ውሳኔዎች ተገዥ ያለመሆን ሕገወጥ ባሓሪ ካለ፤

3ኛ. ምናልባት በአባላቱ መካከል ፅኑ የእምነት ተመሳሳይነት እንኳ ቢኖርም አጠቃላይ የውስጠ ድርጅታዊ ችግሮች አመፍታትና አያያዝ ስልት፤ ልምዱና ብስለቱ ካለመኖር፤

4ኛ. በሂደት የተከሰተን የእምነት ለውጥን/መንሸራተትን መርህን ተላብሶ ኢ-መርሃዊ/ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማስፈፀም መሞከር/ማቀድ በዋናነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ።

እናም አንድነት የውስጥ ችግሮችን ለመፍታት የበለጠ ትኩረት ማድረግ ያለበት ከላይ በጠቀስኳቸው ዐብይ ጉዳዩች ላይ ቢሆን ችግሮች የት ላይ እንዳሉ ለይቶ ለማወቅ ያስችለዋል የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ ባሻገር ግን በውጭ ሆነን ከምናያቸው ለችግሮች ምክናያቶች ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ ከምገምታቸው ድርጊቶች ብነሳ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

1ኛ. አንድነት የመድረክ አባል በመሆን ሕጋዊ አካሄድ ላይ በብሔራዊ ም/ቤት አባላት መካከል ሰፊ የግንዛቤዎች ልዩነት ከነበር?

2ኛ. የአንድነት የብሔራዊ ም/ቤት አባላትና ሌሎች ከድርጅታቸው የተባረሩበት ሁኔታ ሕጋዊ አግባብነት ነበረው ወይ?

3ኛ. አንድነት በመሥራች ጠቅላላ ጉባኤ የመረጣቸውን ከሃያ ያለነሱ ነባር የብሔራዊ ም/ቤት አባላቱን ያለ አስቸኳያ/ወይም መደበኛ/ ጉባኤ ውሳኔ ሲያባርር ሁለት አዲስ አባል የሚላቸውን ለመቀበል ድርጅቱ ጉባኤ ለመጥራት እንዴት የዝግጅት ሓቅም አገኘ?

4ኛ. የአንድነት ውስጠ ደንቡስ በአንድ ጊዜ ያን ያክል ሰፊ ሹመት ለአዲስ አባል ለማሰጠት ይፈቅድለት ነበርን?

የሚሉትን ተራ በተራ እንደሚከተለው ለማየት እሞክራለሁ።

## 1.1. አንድነት የመድረክ አባል በመሆን ሕጋዊ አካሄድ ላይ በብሔራዊ ም/ቤት አባላት መካከል ሰፊ የግንዛቤዎች ልዩነት ከነበር?

ከሁሉ አስቀድመን አንድ በተለምዶ መቀበል ያለብን ሁኔታ ቢኖር ምንጊዜም ቢሆን አንድ ድርጅት ለነደፍኩት ድርጅታዊ ፕሮግራም ተግባራዊነት ይረዳኛል ብሎ ካመነበት ድርጅት ጋር *በተለያዩ*

*የግንኙነት ደርጃዎች ተቀራርቦ ሊሰራ ይችላል። የግንኙነቱ ደረጃ ግን እንደየድርጅቶች አደረጃጀት ባሓሪና ራዐይ አንድነትና ልዩነት የጠበቀና የላላ መሆኑ ግን ፍፁም መረሳት የለበትም።*

ከዚ እምነት በመነሳት አንድ ሰፊ መሰረት ያለው ድርጅት ተመሳሳይ ሕብረ-ብሔራዊ አደረጃጀትና ጠንካራ አቋም ካላቸው ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ መስራት የግድ የሚለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን *በብሔር ደረጃም ከተደራጁት ጋርም እንኳ ቢሆን ከሰፊ ድርጅታዊ አደረጃጀቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት በሚገባ ነድፎ ወደሱ ማቅረብ መቻል ተገቢነት ብቻም ሳይሆን የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ ብስለትንም ጭምር የሚጠይቅ መሆኑ መረሳት የለበትም። በተለይ በወያኔ የጎሠኝነት ልክፍት ሰለባ የሆኑት ሁሉን ከሚጎዳ ድርጊታቸው ታቅበው ወደ ትክክለኛው የትግል አቅጣጭ እንዲገቡ ማድረግ መቻል ራሱ አንዱ የሰፊ መሠረት ትግል አካል በመሆኑ ጭምር።*

*በሌላ መልኩ ግን አንድ ሕብረ-ብሔር ድርጅት በሰመ ትብብር /ወይም ሕብረት/ ስም ከጥንፈኛ የብሔርና የጎሣ አደረጃጀቶች መካከል ሔዶ ቢሰካ/ቢሰነቀር ሰፊ ድርጅታዊ መሠረቱንና የጥዋት አቋሙን አስረክቦ የሚገባበት ሁኔታ መፈጠሩ ስለሚያሰጋ የግንኙነቱን ደረጃና መጠን አስቀድሞ መለየት ይኖርበታል። ይህን አለማድረግ ግን ግብዝነት ብቻም ሳይሆን ወደፊት ወደራሱ ሊያመጣቸው ወይም እንወክለዋለን ከሚሉት ሕብረተሰብ ማዕከል ሊነጥላቸው የሚችላቸውን የብሔርና የጎሣ ድርጅቶች ሁሉንም ከሚጎዳ የጥፋት ተግባራቸው እንዳይመለሱ የልብ ልብ እንዲሰማቸው ማድረግ ይሆንበታል።*

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ከቅንጅት ድርጅታዊ ሕይወት ብዙ ክህደቶችንና መሰነጣጠቆችን አሳልፎ በሁለት እግሩ ለመቆም በዳዴ የዕዴሜ ደረጃ ላይ የነበረው አንድነት ቅድሚያ የራስን የውስጥ ድርጅታዊ ብቃት የማጠናከርን ወሳኝ ተግባር ወደጎን ተወት በማድረግ *እራሱ ባላቀደውና ባልጀመረው ሠፊ ሳይሆን ጠባብ ሕብረት /መድረክ/ ውሰጥ* ገብቶ ለራሱ የውስጥ ድርጅታዊ ችግር ከመዳረግና በሂደትም በእጅ አዙር በተወሰነ ክልል አካባቢ ተወስኖ እንዲታይ መደረጉ እጅግ በጣም ያሳዘነ ድርጊት ነበር።

As we all remember it, during the May 23, 2010 TPLF’s election time, UDJ was technically and deliberately, or by default, reduced to represent only a specific area seats; needless to mention this sad story!

በተለይ በተለይ “አንድነት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ለምርጫ እጩ/ወኪል ለማቅረብ ማሰቡ እኔም ትግራይ ክልል ሄጄ ልወዳደር ነው ማለት ነዋ?” ብሎ ዶ/ር መሪራ ጉዴና አንድነትን መሳለቂ ሲያደርግ ስሰማ በጣም ተገረምኩ። ዶ/ር መሪራ "እኔም ትግራይ ክልል ሄጄ ልወዳደር ነው ማለት ነዋ?" ብሎ ሲሳለቅ የአንድነት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ለመወዳደር ማሰብ ማለት ልክ እሱ ራሱ በማያውቀውና በማያውቃቸው የትግራይ ሕዝብ መካካል ልወዳደር የማለት ያህል እንደሆን አድርጎ በማያሻማ ቋንቋ በንፅፅር ሊያስረዳን ሞከረ።

ኸረ ለመሆኑ የኦሮሞን ሰፊ ሕዝብ ለዶ/ር መሪራ ጉዴና በግል ሀብትነት/ንብረትነት አሳልፎ/ወስኖ የሰጠ የትኛው ሕግ ነበርና ነው የአንድነት አገር አቀፍ አደረጃጀት በዚያ መልክ እንዲገደብ የተደረገ? የአንድነት መሪዎችስ እንዴት የአንድነት አገር አቀፍ አደረጃጀት በዚያ መልክ መሳለቂያ ሲሆን ምኑ ሊቀርባቸው ነበርና ነው የግለሰብ ጫናን እስከ መቀበል ድረስ የሄዱ? በምርጫ አሸንፎ የተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ማግኘት ደረጃው ሁለተኛ - - -የአንድነትን የአደረጃጀት የድርጅትዊ መርህ ቅድሚያ ማስጠበቅ መቻል ግን ቀዳሚውና ዋነኛው ድርጅታዊ ስውነት ሆኖ እያለ?

ለዚህም ነበር በእኔ እምነት አንድነት ከመድረክ አባል ድርጅቶች ጋር ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ትብብር መፍጠር ከፈለገ እንኳ ሊኖር ይገባው የነበር የግንኙነት ደረጃ "ሁሉም ድርጅቶች ነን የሚሉ ድርጅታቸው ያለውን አደረጃጀት ይዘው በሚፈልጉት የአገሪቷ አካባቢዎችና ማዕዘናት ያለምንም ችግር በነፃ መንቀሳቀስ የሚችልበትን ሁኔታ *እነደ ወያኔ እንዳይገድብ* ከማድረግ ስምምነት ያነሰ" መሆን የለበትም ነበር የሚል እምነት የነበረኝ።

አንድነት ከመድረክ አባልነቱ ያገኘው ድርጅታዊ ምላሽ ቢኖር ወደፊት ደረጃ በደረጃ እየተስተዋለ ይፈጠር የነበረውን መልካምና ሁነኛ መቀራረብን አስቀድሞ የሚያሻክር ከመሆኑ ባሻገር ሕብረ-ብሔራዊ አደረጃጀቱን ጭምር አደጋ ላይ የጣለ መሆኑ መሳት የለበትም። ይህም በመሆኑ አንድነት ከመጀመሪያውኑ የመድረክ አባል የሆነበት ሂደቱና አሰራሩ ሕውን ዴሞክራሲያዊ አሠራርን ተከትሎ ነበርን? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ የግድ ይለናል።

አንድነት ከሌሎች አቻ ድርጅቶች ጋር ሊኖር ስለሚገባ ግንኙነት በአንቀጽ 14 የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባርን በንኡስ አንቀጽ 14.10 ላይ በግልፅ ሲያብራራ "ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሊኖር የሚገባን የትግል ግንኙነት በተመለከተ የብሔራዊ ም/ቤቱን ውሳኔና መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል ይላል"። እኔ እንደሚገባኝ በዙዎቹ የአንድነት ውሳኝ ድርጅታዊ ውሳኔዎች የሚባሉት የሚያልፉት የተሳታፊዎችን 2/3ኛ የድምፅ ድጋፍ መሠረት አድርገው እንድሆን ውስጠ ደንቡ ላይ ያመላክታል። እናም ስንቱ የብሔራዊ ም/ቤቱ አባላት የአንድነትን የመድረክ አባልነት ደገፉው ነበር? ስንቶችስ ተቃወሙ? የሚሉትን መጠየቅና ትክክለኛውን ምላሽ ከራሳቸው የብሔራዊ ም/ቤቱ አባላት ማግኘት ተገቢ ይሆናል።

በአንድነት ድርጅታዊ ትንታኔ መሠረትስ "አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች" ሲባልስ አቻ የሚባሉት ምን ዓይነት የፖለቲካ አደረጃጀት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው? እንደ አንድነት ሁሉ ተመሳሳይ ሕብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ አደረጃጀት ያላቸው ድርጅቶችን ብቻ ወይስ በጎሣ ድሮጅታቸው ፕሮግራም ውስጥ ***"የጋራ ቤታችን የሆነችውን እናት ኢትዮጵያን ለማፍረስ አስበውና አቅደው"*** መገንጠልንም የሚደግፉና በግልፅ ያስቀመጡ እንደ ዐረና ትግራይ ያሉ የጎሣ ድርጅቶችም ጭምር የሚያጠቃልል ይሆናል? አንድነት የመድርክ አባል ሆነ ሲባልስ የተሰጠው ቦታ ከሌሎች አባል ድርጅት ከሚባሉት ጋር በምን ድርጅታዊ መሥፈርት ተመዝኖ/ተሰፍሮ ነው እሱ ራሱ አንድነት በሰፊ ድርጅታዊ አንደረጃጀቱ የቆመላቸውንና የሚታገልላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች /የሕዝባችን ክፍል/ እነወክላለን ከሚሉት /በውስጥ ከሚወክላቸው/ ጋር እኩል ሰባት መቀመጫ ብቻ የተሰጠው? እነዚህና መሰል ጥያቄዎች በወቅቱ ተገቢ ምላሽ ካላገኙ በአንድነት አባላት ዙሪያ ላለመግባባት ምክንያት ቢሆኑ አይገርምም።

ይህን ንሁስ ርዕስ ለመቋጨት ሁለት ጉዳዮችን ላንሳ፡- በወያኔ ምርጫ ሰሞን ወያኔ የአካባቢውን መራጭ ሕዝብ ለማስፈራራት አስቦ በዶ/ር መረራ ላይ የእስራት ዛቻ ሆን ብሎ ይቀሰቅስ ነበርና ለዚህ ዛቻ ምላሽ ይሆን ዘንድ ደግሞ በዶ/ር መረራ የተሰጠው አፀፋዊ ምላሽ "ወያኔ እኔን ቢያስረኝ ቀጣዩን ትግል 30 ሚሊዮን የሚሆኑ ኦሮሞዎች ከዳር ያደርሱታል" በማለት ነበር። የእኔ ጥያቄ - - - ዶ/ር መረራ ኢትዮጵያን ከወያኔአዊ ጎሠኛና አድሎአዊ መስተዳድር ለማላቀቀ እየታጋለ ነው ለሚባለው መድረክ የመጀመሪያው መሪና ከፍተኛ አመራር ሆኖ ሳለ ከ80 ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብ ከጎኑ እንደሚቆምለት በርግጠኝነት መናገር ሲገባው ለምንስ በ30 ሚሊዮን ኦሮሞዎች ላይ ብቻ መተማመን እንደፈለገ የሚያሳየው ነገሩን ሁሉ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ማድረጉን ነው።

ሌላው ድራማ ደግሞ ወያኔ ዐረና ትግራይን በትግራይ ሕዝብ ፊት የበለጠ ለማጥላላት ብሎ "ለመሆኑ ዐረና ትግራይ ወልቃይት-ፀገዴንና ሴትት-ሁመራን ወደ አማራ ክልል ለመመለስ ቃል እንደገባ አውቃችኋልን?"/ሰሚሆም ዶዎ?/ በሚል ባለቀ ሰዓት በብዛት ይበትን ለነበረው በራሪ ወረቀት ምላሽ

ይሆን ዘንድ ደግሞ ዐረና ትግራይ በበኩሉ "የለም አንመልስም! ለምንስ እንመልሳለን?" በሚል ዓይነት በጉዳዩ ላይ ከወያኔ የተለየ አቋም እንደለለው ለማሳየት የሚችለውን ሁሉ ማድረጉን እንገነዘባለን። በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከባብሮና ተጋግዞ በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ ብሎ መድረክን በዋናነት የመሰረተው "ዐረና ትግራይ" ለነ መልስ ዜናዊ "የለየለት ዘር አጥፊ/Ethnic cleansing ተግባር" ያን መሰል ምላሽ መስጠቱ እጅግ በጣም ያሳዝናል!! ይልቁንስ ዐረና ትግራይ ከወያኔ የተለየ ሰፊ አቋም አለኝ የሚል ከሆነ ለዚያ መሰል ወያኔያዊ ቅስቀሳ ተገቢ ምላሽ መስጠት ነበረበት።

ለአብነት ያህል የትግራይ ሕዝብ በወልቃይት-ፀገዴና ሴትት-ሁመራ እንደማኛውም ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ሰርቶ ጥሮ ግሮ የመኖርና ሀብት የማፍራት መብት ያለው ብቻ ሳይሆን በሌላው አካባቢም ቢሆን (ማለትም በጎጃም፤ በወሎ፤ በወለጋ፤ በሲዳሞ፤ በወ.ዘ.ተ) አገሩና ቀየው የመሆን ሙሉ መብት እንዳለው ጭምር ከማሳየት ጎን ለጎን ግን የወልቃይት-ፀገዴና ሴትት-ሁመራ ሕዝብ በዚያ አሳዛኝ መልክ ከቀየውና ከሰፈሩ በወያኔ ጎሠኝነት የሚፈፀምበትን ማፈናቀልና ማሳደድ በፅኑ እንደሚቃወመው "ዐረና ትግራይ" አስረግጦ መናገር ነበረበት። ይህን አለማድረግ ግን ዐረና ትግራይን ግምት ውስጥ የሚጥለው ብቻ ሳይሆን የመድረክንም መሥራቾች ውስጠ ባሓሪያት በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሚያሳይ ይሆናል። ይህን የበለጠ ቀረብ ብሎ ለማየት ይቻል ዘንድ “TPLF’s Behavioral Tree Structure” በሚል ከስር ያስቀመጥኩትን ዲያግራም በአጭሩ እንመልከት፤-

“TPLF’s Behavioral Tree Structure”



## 1.2. የአንድነት የብሔራዊ ም/ቤት አባላትና ሌሎች ከድርጅታቸው የተባረሩበት ሁኔታ ሕጋዊ አግባብነት ነበረው ወይ?

የአንድ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ድርጅታዊ ብቃቱ ከሚለካባቸው ዋነኛ መስፈርቶች መካከል አባላቱ በደርጅታቸው ውስጥ ያላቸውን መብትና ግዴታን ባልተዛነፈ መልኩ የሚያስከብር የመሆኑ ጉዳይ ቀዳሚው መሆኑ ነው። የአባላቱን ድርጅታዊ መብትና ግዴታ በአግባቡ የማያስከብር ድርጅት ስለ ሕዝብ መብትና ግዴታ ቆሜአለሁ ቢል ከቶ የሚታመን አይሆንም። አንድ ግለሰብ የድርጅትን ፕሮግራምና ውስጥ ደንብ አምኖ እስከተቀበለ ድረስ የድርጅት አባል ለመሆን መንገዱ በጣም ቀና የመሆኑን ያህል እሱን ከድርጅታዊ ሰውነቱ ለመነጠልና ለማባረር ግን ተጨባጭ ምክንያትን ከማግኘት ባሻገር ብዙ የድርጅት አሰራር ሂደትን ተከትሎ ማስፈፀምን የግድ ይላል።

በተለይ ችግሩ የተከሰተው በከፍተኛው የአመራር ማዕከል ውስጥ ከሆነ በየትኛውም ድርጅት ውስጥ ይሁን ለተወነ ጊዜ በ2/3ኛ ወይም 3/5ኛ ድምፅ ካሉበት መደበኛ የድርጅት ኃላፊነት ከሥራ ማገድ የሚቻል ቢሆንም ያለ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከድርጅት ማባረር የማይቻልበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህ የሚሆንበት ዐብይ ምክንያት በአንድ ድርጅት ውስጥ አባልን/ወይም አባላትን/ ከድርጅት ማባረር እጅግ በጣም ከፍተኛው ድርጅታዊ ቅጣት በመሆኑ ነው።

እርግ ነው ለአንዳንዶቹ - - - የድርጅት ሕይወት ምንነት ለማይገባቸው - - - የድርጅትን አባላት በፈለጉት ጊዜ ያለምንም ስጋት ማባረር በጣም የሚቀላቸውን ያህል ለአንዳንዶቹ ደግሞ አባሎቻቸው በዕድሜ መግፋት፤ በጤና ጉዳይ አልያም በቤተሰብ ችግር ምክንያት ከሚወዱት ድርጅት ወደኋላ በማለት ከድርጅት ተሰናብተው ሲሄዱ እንኳ በእምባ እስከ መራጨት ድረስ ይኬዳል።

በእኔ እምነትና ድርጅታዊ ልምድ እንደሚታየኝ ከሆነ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ያለቸው አገራችን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ድርጅት የውስጥ ድርጅታዊ ችግሮችን በመግባባትና በድርጅት ውስጠ ደንብ መርህ መሠረት በሰፊና ዴሞክራሲያዊ ውይይት እየፈታ የሚሄድ ድርጅታዊ ሰውነት ያለው ድርጅት እንጅ በሆነ ባልሆነው እርስ በእርሱ የሚወነጃጀሉ አባላት ያሉበትና አንዱ አባራሪ ሌላው ተባራሪ የሚሆኑበት ዓይነት ድርጅት አይደለም። ይህ በአስቸኳይ መቆም አለበት። ከሃያና ከዚያ በላይ በአንድ ጊዜ ከመሠረቱት ድርጅት መባረር አይደለም ያንድ ሰው ወደኋላ ተነጥሎ መቅረት እንኳ በጣም ሊሰማን ይገባል።

አንድነት አባላት የሚባረሩበትን ሁኔታ በውሰጠ ደንቡ በአንቀጽ 8 "አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች" በሚል ስር በንኡስ አንቀጽ 8.3 ላይ በግልፅ ሲያብራራ "በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ለመወሰን *ሥልጣን ባለው አካል* ከአባልነት እንዲወገዱ ሲሆን ነው" ይላል። የአንድነት የብሔራዊ ም/ቤት አባላት የተባረሩት እውን እነሱን ሊያባርር በሚችል *ሥልጣን ባለው አካል ነበርን? የአባራሪው የሥልጣል አካልስ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚያንስ ሆነና ነው በብሔራዊ ም/ቤት ብዙሓን ውሳኔ መባሉ? መልሱን ለአንድነት አባላት ሕሊናዊ ፍርድ እተወዋለሁ።*

*በተለይ በተለይ ሰፊ የድርጅታዊ አሠራር ልምድ እንዳለው ታምኖበት በአንድነት አመራር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው አቶ ሰዬ አብርሃ ስለ አንድነት የውስጥ ችግር ጉዳይ በvoa የአማርኛው ክፍል በቅርቡ ቀርቦ በተጠየቀ ጊዜ "በብዙሓን ውሳኔ ተባረሩ" ማለቱ እውን ያ የብዙሓን ውሳኔ የሚባለው ከሃያ የሚበልጡ መሥራች አባላቱን ማባረር የሚያስችል ሥልጣን የነበረው አካል ነበርን? ለመሆኑ ወያኔ በራሱ ላይ የፈፀመውን ሕገ-ወጥ የማባር አካካሄድ ከመቸው ረሳው? እንዲያውም በእኔ እምነት አቶ ሰዬም ሆነ ዶ/ር ነጋሦ ወደ አንድ ወገን ከመወገን ይልቅ ሁለቱንም የአንድነት አካሎች በሽምግልና መልክ በማቀራረብ አስቸኳይ እልባት ያደርጉ ይሆናል የሚል ተስፋ ነበረኝ። ያን*

*ባለማድረጋቸው ግን እንዲያው አገራችን የአገር መሪም ብቻ ሳይሆን ሽማግሌም ጭራሽ አጣች እስከማለት ድረስ ሄድኩ።*

## 1.3. አንድነት በመሥራች ጉባኤ የመረጣቸውን ከሃያ ያለነሱ ነባር የብሔራዊ ም/ቤት አባላቱን ያለ አስቸኳያ/ወይም መደበኛ/ ጉባኤ ውሳኔ ሲያባርር ሁለት አዲስ አባል የሚላቸውን ለመቀበል ድርጅቱ ጉባኤ ለመጥራት እንዴት የዝግጅት ሓቅም አገኘ?

የአንድነት መሥራች አባላቱን በተለይም ከሃያ የማያንሱ የብሔራዊ ም/ቤት አባላት ያለ አስቸኳይ/ወይም መደበኛ/ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ከአንድነት በተባረሩ ማግሥት አንድነት ሁለት አዲስ አባላቱን ጉባኤ ጠርቶ ለመቀበል ምን አቅምና አሳማኝ ምክንያት አገኘ? በብሔራዊ ም/ቤት ውስጥ የጎደሉ ክፍት ቦታዎች ካሉ እንኳ ካሉት 15 ተጠባባቂ የብሔራዊ ም/ቤት አባላት ውስጥ ባገኙት ድምፅ ቅደም ተከተል መሠረት ራሱ ብሔራዊ ም/ቤቱ ስቦ/አምጥቶ/ መሙላት እንደሚችል ውስጠ ደንቡ የሚፈቅድ ቢሆንም መሥራች ጠቅላላ ጉባኤ የመረጠውን የብሔራዊ ም/ቤት አባላት አባሮ አዲስ የብሔራዊ ም/ቤት አባላትና የሥራ አሥፈፃሚ አባላትን ለማስመረጥ የትኛው የውስጠ ደንብ መብቱ ለሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ይፈቅድለታል?

ካዚያ ባሻገርስ ሁለቱን አዲስ አባላቱን ለመቀበል ተጠራ በተባለ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ጉባኤው እግረ መንገዱን በነሱም ላይ የሚወስንላቸውን /ቅጣትም ይሁን ተግሣፅ አላያም እስከ ማባረር የሚደር/ የቅጣት ውሳኔ ለመቀበል አልያም የተበላሸ አሠራርን ለማስተካከል በጉባኤ ላይ ለመገኘት የፈለጉን/ተባረዋል የተባሉትን ማለት ነው/ጉባኤ ላይ እንዳይገኙ መከልከል ለምን አስፈለገ? አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ቁም ነገር ቢኖር ምንም ይሁን ምንም የአንድነት ጠቅላላ ጉባኤ የመረጠውን የብሔራዊ ም/ቤት አባል ከጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ውጭ ከድርጅት አባልነት ማባረር ከቶ የሚቻል አይደለም። ብሔራዊ ም/ቤቱም ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ እንጅ ወደ ታች ወረዶ ለሥራ አሥፈፃሚ አካል አይደለም።

## 1.4ኛ. የአንድነት ውስጠ ደንቡስ በአንድ ጊዜ ያን ያክል ሰፊ ሹመት ለአዲስ አባል ለማስጠት ይፈቅድለት ነበርን?

በአንድ ድርጅት ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን መኖር ያለበት ድርጅታዊ መርህ የድርጅቱ ሥራዎች "ብቃት ባላቸው" ነባርም ይሁኑ አዳዲስ አባላት መሠራት እንዳለበት አምኖ መቀበልን ነው። ይህን ስንል ግን ሌላው መረሳት የሌለበት ተዛማጅ ጉዳይ አባላት ለድርጅታቸው ያላቸው ፅኑ ታማኝነት ከሁሉም የሚልቅ መሆኑ ነው። ለፅኑ ታማኝነታቸው መመዘኛው ሚዛን ደግሞ ድርጅታቸው ባለፈባቸው ውጣ ውረዶች ሁሉ ሳያመነቱ አርያ ሆነው መዝለቅ የሚችሉ መሆኑን ያሳዩ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

ከዚህ አኳያ በአንድነት ውስጥ ከቅንጅት ድርጅታዊ ሕይወታቸው ጀምሮ ብዙ የፖለቲካ በሳልና ፅኑ ድርጅታዊ እምነት ያላቸው አባላት ይኖራሉ ብዬ ስለማምን የአቶ ስዬና የዶ/ር ነጋሦ የአንድነት አባል መሆን ልዩ ቦታ ተሰጦት ሹመት ለማስጠት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስጠራ አልነበረም - - - እነሱ ራሳቸው ቦታ ካልተሰጠን አባል አንሆንም ካላሉ በስተቀር? ይህን ቢሆን መቀበል ስፅተት ነው።

እናም ይህን አካሄድ ራሱ በአንድነት ውስጥ እንደ አንድ የውስጥ ችግር ሰበብ አድርገው የሚያቀርቡ ቢኖሩ ልንፈርድባቸው አይገባም። ምክንያቱም በነሱ ግንዛቤ ችግሩ ሹመቱ ከመስጠቱ ላይ ሳይሆን በድርጅት የአሠራር መርህ ሊያዩት ይችላሉና። የአንድነት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በአንድነት ውስጥ የተፈፀረውን የውስጥ ችግር ለመፍታት ነገሮችን በቅንነት፣ በውስጠ ደንቡ ትክክለኛ አግባብና በሰከነ ሕሊና ማየት ይኖርበታል። ችግሮችን ከሥሜት ነፃ በሆነ መልኩ ለመፍታት እድሉ ያለው በእጃቸው

ነው። በእዳጀቸው ያለውን እድል ሳይጠቀሙ ቀርተው የውስጥ ችግራቸውን እንዲዳኙላቸው የወያኔ ፍርደ ገምድልን ዳኝነት መጠበቅ እጅግ በጣም የሚያስቅ ብቻ ሳይሆን በጣም ያሳዝናል/ ያስተዛዝባል።

ምንም እንኳን ከላይ በተወሰኑት የመድረክ አባል ድርጅቶችና በአንድነት መካከል ያልውን ስፊ ያደረጃጀት ልዩነት ለማሳየት ብሞክርም ከመድረክ አባል ድርጅቶች ጋር የተፈጠረው መልካም ግንኙነት የበለጠ የሚጎለብትበትና ወደ ተሻለ የእድገት ደርጃ የሚደርስበት መንገድ ነው መቀየስ ያለበት እንጅ አሁን ያለውን መልካም ግንኙነትና ትብብር እንደገና ወደ ኋላ መጎተት ለማንም አይጠቅምም። በዚህ ረገድ አንድነት የሚጠበቅበትን ሠፊ የማጠናከር ሥራ ለመሥራት ያስችለው ዘንድ ግን መጀመሪያ/ቅድሚያ/ በራሱ ዙሪያ ባሉ የውስጥ ድርጅታዊ ችግሮች ሁሉንም /የቀድሞና አዲስ/ አባላቱን ባካተተ ሰፊና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ባስቸኳይ ፈቶ እንደ አንድ ጠንካራና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ኃይል ቆሞ መታየት አለበት። *ቀጣዩም ትግል ይህ መሆን ይኖርበታል።*

አንድነት ከመድረክ አባል ድርጅቶች ጋር ማድረግ ያለበት ግንኙነትም ሕብረ-ብሔራዊ አደረጃጀቱን ጠብቆና አጠናክሮ ቅንና አርያነት በተሞላበት ትብብርና ዴፐሎማሲያዊ ሥራ ሌሎች የመድረክ አባል ድርጅቶችን ወደራሱ ሰቦ በማምጣት በጠንካራዋ ብርቱካን የሚመራ አገር አቀፍ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ኃይል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማቀረብ ይጠበቅበታል። የመድረክ አባል ድርጅቶችም ከወያኔአዊ የጎሣ ፖለቲካ ሰለባነት ራሳችውን አላቀው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመከባበርና በዴሞክራሲያዊ እኩልነት የሚኖርባትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ወደ ሠፊ አገር አቀፍ አደረጃጀት መምጣት የግድ ይኖርባቸዋል። ይህ የማሆን ከሆነ ግን አሁንም ቢሆን አገራችን ከወያኔ የጥፋት ተልዕኮ ማላቀቅ ከቶ የሚቻል አይሆንም።

በመጨረሻም ምስጋና አሜሪካ/በተለይ ዋሽንግተን ዲሲ/ ላሉ ኢትዮጵያዊያን ዲዮስጶራ፡- አሜሪካ ያለው ኢትዮጵያዊ ዲዮስጶራ በአገሩ ጉዳይ ላይ ምን ጊዜም ግንባር ቀደም መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ አሳይቷል። በቅርቡ ደግሞ በጁን 27/2010 ለታማኝ በየነ የተደረገውን የአክብሮት ዝግጅት እጅግ በጣም ስሜትን በሚነካ መልኩ ከቪዲዮ ሴግመንት ላይ ሳይ እናንተ የታማኝን መልካም ሥራ ስታከብሩ እኔ ደግሞ እናንተን ውለታ ከፋይነት አደነቅኩ። ስለታማኝ በየነ ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት እኔ የምለው የለኝም --- ሁሉም ስለሚያውቀው። ብቻ አንድ ነገር ላስታውሳችሁ። የዛሬው ለሕዝብ ውሳኔ አልገዛም ባዩ መንሥት የያኔ መራሹ ወያኔ "በዚህ ቀን ይህን ያህል ሸ የደረግን ወታደር ገደልኩ፤ በዚህ ቀን ይህን ይህል ገደልኩ፤ ወ.ዘ.ተ" እያለ የሚለው የወያኔ የግድያ ዜና ታማኝን ይገርመውና ብሔራዊ ትያትር ቤት በጨዋታ መካከል መድረክ ላይ ይዞ ይቀርብና እንዴት ነው ወገን? "ወያኔ ገደልኩ የሚለውን የሠራዊ ቁጥር ብንደምረው አገሪቷ አሁን ካላት የሠራዊ ቁጥር ይበልጣል ታዲያ ቀሪውን የሚች ቁጥር የምንከፍለው ተበድረን መሆኑ ነው? ብሎ ሰቆ ማሳቅ በሚያውቅበት አንደበቱ ታዳሚውን ሕዝብ እንዳስቀ ከሩቅ ሰማንና ለካ ታምኝ አርቲስት ብቻም ሳይሆን የቅኔም ሰው ነው ብለን በማዘር-ላንድ (Motherland) ልሣን በብሥራተ-ዴሞክራሲ ወቅታዊ በራሪ ጽሁፍ እንደ አገራችን አቆጣጣር በ1984 ስጋቱን ለሕዝባችን ግልፅ አደረግንለት።

ያ የታማኝ አይቄሬ ስጋት የኾውና ዛሬ ይበልጥ ግልፅና እውን ሁኖ ወያኔ የገደለው የደርግ ሠራዊት የሚባለውን ብቻ ሳይሆን ይህን የዛሬውንና ገና መጭውን ትውልድ እንደዚሁም የሁላችንም እናት የሆነችውን ኢትዩጵያ ጭምር የሚገድል ተግባር እየፈፀመ ነው። ታማኝ - - - ገና ተበድረን የሞትን እዳ ልንከፍል ነዋ? ብሎ በጥርሱ ሰቆ በልቡ አዝኖ ሊያስጠነቅቀን የሞከረም ይህን ስጋቱን ነበር! ታማኝ ገና በወጣትነቱ እድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ ከወያኔ ጋር በየመንገዱ ግብ ግብ ሲያያዝ የኛ ምሁር ተብዮዎች ግን የወያኔ ደሞዝተኛ ለመሆን ወይም ሊነግዱ አቅደው ከውጭ አገር ቆይታቸው ወደ ሀገር ቤት ይመለሱ እንደነበር አይረሳም።